ሀምሌ 21, 2020

ውድ የ OSS ማህበረሰብ፣

ወደፊት እያየን እና ለ 2020 - 2021 የትምህርት ዓመት እየተዘጋጀን ባለንበት ወቅት፣ የ COVID-19 ወረርሽኝ ባለበት ሁኔታ  በመጋቢት ውስጥ በፍጥነት ወደ የርቀት ትምህርት ስንዘዋወር ፣ ለተለዋዋጭነትዎ እና ከሁኔታዎችዎ ጋር ተጣጥሞ ለመላመድዎ ጥልቅ ምስጋናችንን ለመግለጽ እንፈልጋለን። ይህ ሽግግር ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ያስከተለ ብስጭት እና ግራ መጋባት ይሰማናል ፣ እናም በዚህ ውጣ ውረድ ወቅት ሁሉ  ወቅታዊ ግንኙነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን። በዚህ ምክንያት እኔ ሆንኩ ቡድናችን ልጅዎን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ ቀደም ተከተሎቻችንን እና ልምዶቻችንን እንደገና ለማደስ በአካል ፣ ሙሉ ለሙሉ ከርቀት ወይም የሁለቱመ ጥምረት መሁኑን ፣ በዚህ ክረምት በጋራ እየሰራን እንገኛለን። ይህ በዚህ አዲስ የመማሪያ አካባቢ ውስጥ ለመተባበር የበለጠ መደበኛ ግንኙነቶችን እና ተጨማሪ ዕድሎችን በውስጡ ያካትታል።

ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንደነበሩ እናውቃለን ፣ እናም እንደቻልነው ሁሉንም እናስተናግዳለን። እባክዎን ከዚህ በታች ያለን የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ያግኙ:

1. የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል (DESE) ለአካል ጉዳተኞች ተማሪዎች የመኸር ጊዜ መመሪያ- በመጀመሪያ ፣ ሙሉ ሰዓት ለሁሉም ተማሪዎች የማይቻል ከሆነ ፣ DESE ለአካለ ስንኩላን በተለይም  ለቅድመ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና አስፈላጊ እና ውስብስብ ፍላጎቶች ላላቸው የአካል ጉዳተኛ ትምህርት ቅድሚያ እንዲሰጡ ወረዳዎችን ጠይቋል። ለእነዚህ ተማሪዎች ሙሉ ጊዜ የማይቻል ከሆነ ፣ የትምህርት ቤት ወረዳዎች በተቻለ መጠን ብዙ በአካል የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ለተማሪዎቻቸው በትርፍ ሰዓት ላይ እንዲሰጡ ይበረታታሉ (ማለትም ተዛማጅ ሕክምናዎች ፣ ABA እና የማህበራዊ-ችሎታ ቡድኖች)። አንድ ቤተሰብ የርቀት ብቻ አማራጭ ከመረጠ ፣ ወይም ለሁሉም ተማሪዎች በርቀት እንዲማሩ በመላ-ስቴት ወይም በአካባቢ ግጼታ ካለ ፣ ከዚያም ትምህርት ቤቶች እና ወረዳዎች በተማሪው IEP ላይ በተጠቀሰው መሠረት “መመርያ እና አገልግሎቶች” በሚለው የማድረስ ሞድ አገልግሎቶችን ለማቅረብ መዘጋጀት አለባቸው።

2. OSS የቤተሰብ ጥናት፤ በፀደይ ወቅት ስለ እርስዎ እና ስለ ልጅዎ የርቀት ትምህርት ተሞክሮ የበለጠ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ በዚህ ሳምንት ሰኞ ዕለት ልከናል። ይህ ሽግግር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደ ሆነ እናውቃለን ፣ እናም ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ የርቀት የመማር ዕድሎችን መፍጠር እንድንችል የእርስዎ ግብረ መልስ ለክረምት ዝግጅታችን ወሳኝ አካል ነው። እባክዎን ይህን አጭር ጥናት ከሰኞ እስከ ጁላይ 27 ድረስ ያጠናቅቁ። እርዳታ ከፈለጉ እባክዎን በ cps@cpsd.us ወይም በ 617.349.6494 ያግኙን።

3. ወርሃዊ የቨርቹዋል ከተማ ስብሰባዎች፣ ከሐሙስ ሐምሌ 30 በ 3: 00 pm ጀምሮ የሚጀምሩ ወቅታዊ የቨርቹል ከተማ ስብሰባዎችን አዘጋጃለሁኝ። እባክዎን እንድንወያይበት የሚፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄ እዚህ ያስገቡ። በዝግጅቱ ላይ ስለሚኖሩት ዝርዝሮች ከመድረሻ አገናኝ(link)  ጋር እናቀርባለን።

በአጋርነት,

ዶክተር አሌክሲስ ሞርጋን

ረዳት ተቆጣጣሪ ፣ የተማሪ አገልግሎቶች ጽ/ቤት